# “ቀን ሳለ . . .”

መድኃኒታችን ኢየሱስ ሥጋ ለብሶ ወደ ምድር የመጣው ስለ ኃጢያታችን ለመሞት ብቻ ሳይሆን በስሙ አምነነ የዳንን እኛ በምድር ልንኖር በቀረልን ዘመን እንዴት ማሰብ፤እንዴት መሥራትና አንዴት መኖር እንዳለብን እናውቅ ዘንድ ሕያው ምሳሌ ሊያኖርልን ነው፡፡ ዱካውን ተከትለን በሕይወት ጎዳና ልንገሰግስ ከወደድን ወንጌላት አስደናቂ ብርሃን ባረገዙ ሕያው መልዕክቶች ተሞልተው ይጠብቁናል፡፡ ሁሉን በአንዴ ማየት ባይቻለን እንኳ ከዮሐንስ ወንጌል ሁለት ክፍሎች ወስደን ለማየት እንሞክር፡፡
እነዚህ ክፍሎች በዮሐንስ ወንጌል 9 እና 11 የሚገኙ ሲሆን እንዳቀማመጣቸው በቅደም ተከተል እናያቸዋለን፡፡
አንድ ቀን ጌታ ኢየሱስ ከደቀ-መዛሙርቱ ጋር በመንገድ ሲሄድ ከመወለዱ ጀምሮ እውር የነበረ ሰው አየ፡፡ ደቀ-መዛሙርቱም አዩ፡፡ ምንም እንኳ ሁሉም ያዩት አንድ ነገር ቢሆንም ያዩትን የተረጎሙበት መንገድ ለየቅል ነበር፡፡ ደቀ-መዛሙርቱ ኃጢአት አዩ ወዲያውም ‹‹ይህ ሰው እውር ሆኖ እንዲወለድ ኃጢአት የሰራ ማነው? እርሱ ወይስ ወላጆቹ?›› በማለት ጥያቄ አነሱ፡፡ በእርግጥ ይህን ሃሳብ ከራሳቸው አላፈለቁትም፣ በዙሪያቸው ያሉ የአይሁድ መምሕራን አንድ ሰው አካለ ጎዶሎ ሆኖ ሊወለድ የሚችለው ከወላጆቹ ኃጢአት የተነሳ እንደሆነና አንዳንዴም ፅንሱ ራሱ በማህፀን ውስጥ እያለ ኃጢአት ሊፈፅም እንደሚችል ያስተምሩ ነበር፡፡ (ዮሐ. 9:34 ይመልከቱ) ምንም እንኳ ደቀ-መዛሙርቱ አይነ ስውሩን ሲያዩ የታያቸው ኃጢአት ቢሆንም ጌታ ኢየሱስ ግን ያየው በዚህ ሰው መፈወስ የሚገለጠውን የእግዚአብሔር ሥራ ነበር፡፡ ስለዚህ ቆም አለና ጭቃ በምራቁ አርሶ ዓይኑን በመቀባት በሰሊሆም መጠመቂያ እንዲታጠብ ላከው፡፡ በውጤቱም ዓይነ ስውሩ አይናማ ሆኖ ተመለሰ፡፡ ጌታ ይህንን ያደረገው አንድ ማየት የተሳነው ሰው እንዲያይ ለማድረግ ብቻ ሳይሆን የብዙዎች የልብ ዓይን በርቶ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በማመን ሕይወት እንዲያገኙና በተቃራኒው የብዙዎች የልብ ዓይን ሊፈወስ እስከማይችል ድረስ መታወሩን ልባቸውም መደንደኑን ለማሳየት ነው፡፡ ይህ እውነት ኢየሱስ ከተወለደ ከጥቂት ቀናት በኃላ እንደ ሕጉ ሥርዓት ለመፈፀም ወደ ቤተ-መቅደስ ሲወስዱት በመቅደስ በር ላይ ያገኘውና የታቀፈው ስምዖን በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ በተለይ ለማርያም የተናገረውን ቃል ያስታውሰናል፡፡

> ‹‹እነሆ የብዙዎች ልብ ሃሳብ ይገለጥ ዘንድ ይህ በእስራኤል ላሉት ለብዙዎቹ ለመውደቃቸውና ለመነሳታቸው ለሚቃወሙትም ምልክት ተሾሞአል. . . ››
> ሉቃስ 2፡-34፣35

አይሁዳውያን በውጭ ኃይማኖተኞች መስለው ስለሚታዩ የእነማን ልብ ለዘላለም ሕይወት እንደተዘጋጀ የእነማን እንዳልተዘጋጀ ለማወቅ እጅግ አስቸጋሪ ነው፡፡ ሆኖም ጌታ ያከናወናቸው ተዓምራቶች የተሰወረውን የልባቸውን ሁኔታ ለመግለጥ ልዮ ኃይል ነበራቸው፡፡ ለዚህ ነው ዮሐንስ በወንጌሉ ተአምራቶቹን ‹‹ምልክት›› እያለ የሚጠራቸው፡፡ ተአምራቶቹ ይህንን ተግባር የሚያከናውኑት በድንቃ ድንቅነታቸው ብቻ ሳይሆን አከራካሪና አነጋጋሪ በመሆናቸው ጭምር ነበር፡፡ እንደሌሎቹ ተዓምራቶች ሁሉ ጌታ ይህን ዓይነ ስውር የፈወሰው በሰንበት ቀን ነበር፡፡
ጌታም ‹‹የእግዚአብሔር ሥራ በእርሱ ይገለጥ ዘንድ ነው›› ያለው የእርሱ መፈወስ ከእርሱ ባሻገር የብዙ አይሁዳውያንን ልብ ስለሚገልጥ ነበር፡፡ ይህንንም በምዕራፉ መጨረሻ ከሰፈረው የጌታ ንግግር መገንዘብ እንችላለን፡፡

‹‹ኢየሱስም፡- የማያዩ እንዲያዩ የሚያዩም እንዲታወሩ እኔ ወደዚህ ዓለም ለፍርድ መጣሁ አለ፡፡›› ዮሐ. 9፡ 39

ቀኑ አይሁዳውያን ፈፅሞ የማይሰሩበት የሰንበት ዕረፍት መሆኑ ቢታወቅም ጌታ ግን እውነተኛው ሰንበት ከሳምንቱ ቀናት የመጀመሪያው ቀን ሳይሆን ሰው በእርሱ ሥራ የሚያገኘው ዕረፍት እንደሆነ ለማሳየት ያለምንም ማመንታት ወደ ሥራ ገባ፡፡
ጌታ ኢየሱስ በሰንበት ለምን እንደሚሰራ ሲያስረዳ የሰጠው ምክንያት ‹‹የምሰራው የሥራ ቀን ስለሆነ ነው፡፡ የሰው ሕይወት የሚከፈለው ሰንበትና አዘቦት በሚል ሳይሆን ቀንና ሌሊት በሚል ነው፡፡ ቀንና ሌሊትን የሚለየው ብርሃንና ጨለማ ነው፡፡ ብርሃን ካለ ቀን ይባላል፤ ሰውም እንደልቡ ይንቀሳቀሳል ሥራም ይሰራል፤ ብርሃን ሲሄድ ግን ጨለማ ይተካል ከጨለማውም የተነሳ ወዲህ ወዲያ መንቀሳቀስና መሥራት ስለማይቻል ሰው ሁሉ ወደ ቤቱ ይገባል ሥጋውንም ያሳርፋል፡፡ በጨለማ የሚሰሩ ካሉ እነርሱ ሌቦችና ክፉ አድራጊዎች ብቻ ናቸው፡፡ አሁን ደግሞ ብርሃን ስላለ ቀን ነው፡፡ ቀን ከሆነ ደግሞ የላከኝን ሥራ ልሰራ ይገባኛል›› ማለቱ ነው፡፡ ይህ ኢየሱስ የሚለው ቀን ምንድነው? ሌሊቱስ? ይህ ቀንና ሌሊት እኛ ከምናውቀው የ24 ሰዓት ቀንና ሌሊት የተለየ ነው፡፡ እንደምናውቀው ቀንና ሌሊት የሚለዩት በአንድ ነገር ብቻ ነው፡፡ እርሱም ብርሃን ነው፡፡ ብርሃን ካለ ቀን ነው፤ ብርሃን ከሌለ ደግሞ ጨለማ ነው፡፡ ቀን ሲሆን ሰዎች ያለመሰናከል ይመላለሳሉ፤ ብርሃን በሌለበት የሚመላለሱ ደግሞ ይሰናከላሉ፡፡

ጌታ ኢየሱስ በምድር የነበረበትን ዘመን ቀን ብሎ ይጠራው ነበር፡፡ ቀኑም የተፈጠረው ብርሃን የሆነው እርሱ በሰው ልጆች መካከል በመገኘቱ ነው፡፡ ይህ ቀን ምንም እንኳ ከሌሎች ቀኖች በተለየ ረዥም ቢሆንም ሁሌ የሚኖርና ቆሞ የሚጠብቅ ቀን አልነበረም፡፡ በዝግታም ቢሆን የብርሃኑ ምንጭ የሆነው እርሱ መሄዱና ከዓለም አይን መሰወሩ የማይቀር ነበርና ጨለማው እየቀረበ እንደነበር እሙን ነው፡፡
ጌታ ኢየሱስ ይህን ዓይነ ስውር ሲፈውስ አገልግሎቱን ከጀመረ ሦስት አመት ሆኖታል በመስቀል ላይ ሊሞትና ከዚህ ዓለም ሊሄድ የቀረው ጊዜ ስድስት ወር ብቻ ነበር፡፡
አጠቃላይ የአገለግሎቱ ዘመን ሰባት መንፈቅ ነበር ብንል ከሰባቱ ስድስቱ ተገባዶ የቀረው አንዱ ብቻ ነበር፡፡ አይሁድ ሕጋቸውን ተከትለው ‹‹ሰንበት›› ነው፤ የእረፍት ጊዜ ነው ቢሉም እርሱ ግን ‹አይ! የሥራ ቀን እንጂ ዕረፍት አይደለም፤ ይልቅ የዕረፍት ጊዜ ወደፊት ነው› በማለት ወደ ሥራ ውስጥ ሲገባ እናያለን፡፡
በእርግጥ ከዚህ ቃል ብርሃን አንፃር ስንመለከት ሊጨልም የቀረው ጊዜ ጥቂት ቢሆንም ሙሉ በሙሉ አልጨለመምና የሥራ ጊዜ ነበር ማለት ይቻላል፡፡
ቀኑ የጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ መሆንና የእግዚአብሔርን ሥራ መስራት ከሆነ፤ ሌሊቱስ ምንድን ነው? ብለን መጠየቃችን አይቀርም፡፡
ከጥቂት ጊዚያት በኃላ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ይሞታል፤ ከዚያም ይነሳል ከዚያም ወደ አባቱ ይሄዳል፡፡ ከዚህ ጊዜ በኃላ ዓለም አያየውም ስለዚህ ለዓለም እንደቀድሞው በቀጥታ ማብራት ያቆማል ማለት ነው፡፡ ማብራቱን ማቆሙ ደግሞ በዓለም ላይ ጨለማን ያስከትላል፡፡ (ዮሐ. 14፡19 ይመልከቱ)
ታዲያ ማብራቱን ያቆማል ስንል ዓለም ብርሃኑን ማየት ታቆማች ማለታችን እንጂ እርሱ ብርሃኑን መስጠት ያቆማል ማለታችን አይደለም፡፡ እርሱ ብርሃን ነውና አለማብራት አይችልም፡፡ ሆኖም ከእርሱ መሄድ የተነሳ ይሄኛው ዓለም ይጨልምበታል እርሱ ግን በመንፈሳዊው ዓለም በአባቱ ቀኝ ሆኖ ማብራቱን ይቀጥላል፡፡ በመንፈስ ከእርሱ ጋር የሚጣመሩና በስሙ በማመን ከጨለማው ሥልጣን ወደ ፍቅሩ ልጅ

መንግስት የሚፈልሱ ሁሉ የቅዱሳን ርስት የሆነውን ብርሃን ይካፈላሉ። (ቆላስያስ 1፡12-14 ይመልከቱ)

ፀሐይስ ሲመሽ ማብራቷን ያቆመች ይመስል የለ! ሆኖም አንደኛው የአለም ክፍል ሲጨልምበት ሌላኛው ቀን ወጥቶለት በብርሃን እንደሚመላለስ ሁሉ የጌታም ከዚህ ዓለም መሄድ ይህኛውን ቢያጨልመውም በዚያኛው ዓለም ማብራቱን ይቀጥላል።

በዚህ ምድር ሳለ ግን ብርሃን ነበርና የነበረበትን ጊዜ ሁሉ ‹‹ቀን›› ብሎ ጠርቶታል።

ብርሃኑን አይተው፣ መንጋቱን ተረድተው፣ በብርሃኑ ሊመላለሱ ያልወደዱትን ይልቅ የልባቸውን በር ዘግተው ገና ጨለማ ነው፣ አልነጋም ለሚሉት የአይሁድ ሕዝብ፡-

> ‹‹ገና ጥቂት ጊዜ ብርሃን ከእናንተ ጋር ነው። ጨለማ እንዳይደርስባችሁ ብርሃን ሳለላችሁ ተመላለሱ። በጨለማም የሚመላለስ ወዴት እንዲሄድ አያውቅም። የብርሃን ልጆች እንድትሆኑ ብርሃን ስላላችሁ በብርሃን እመኑ።›› ዮሐ 12፡ 35-36

እያለ ይማፀናቸው ነበር። እነርሱ ግን አላመኑም። ያላመኑትም ስለመንጋቱና ብርሃን ስመለውጣቱ በቂ ማረጋገጫ ስላላገኙ ሳይሆን ማየት እንዳይችሉ የልባቸው አይን በመታወሩ ነበር። (ዮሐ. 12፡37-41 ይመልከቱ) ለታወረ ሰው ቀኑም ሌሊቱም አንድ ነው። የብርሃንን ገጽታና ውበት፣ የድምቀቱን ክብርና ግርማ፣ ለሚመለከተውም የሚፈጥረውን የደስታ ስሜት ለታወረ ሰው እንዴት መግለጥ ይቻላል?

ለኢየሱስ ግን በምድር መኖር በዙሪያው ላሉት ሁሉ ቀን መፍጠር፣ የቀን ምክንያት መሆን ነበር። ጌታ በቀጥታ የዓለም ብርሃን ለመሆን በምድር መኖር ነበረበት። ለዚህ ነው በዓለም ሳልሁ የአለም ብርሃን ነኝ ያለው።
ጌታ ኢየሱስ በዚህ ንግግሩ ሌሊትን ሲገልጽ ‹‹ማንም ሊሰራበት የማይችልባት ሌሊት ትመጣለች ብሏል።›› ምን ማለቱ ነው?
አስቀድሜ እንዳልኩ ጌታ ቀን ያለው የምድር የሕይወት ዘመኑን ነው። ልክ በሥጋ ሲሞት ለአለም ማብራቱን አቆመ። ብርሃኑን የሚያንፀባርቅበት ሥጋው ብርሃን ከሆነው ሕይወቱ ተለይቷልና። በመስቀል ላይ መንፈሱ ከሥጋው ሊለይ ሲቃረብ በምድር ላይ የተከሰተው ነገር የዚህ እውነት ማረጋገጫ ነበር።

> ‹‹ከስድስት ሰአትም ጀምሮ እስከ ዘጠኝ ሰአት ድረስ በምድር ሁሉ ላይ ጨለማ ሆነ። . . . ኢየሱስም ሁለተኛ በታላቅ ድምጽ ጮሆ ነፍሱን ተወ።››
> ማቴ 27፡ 45፣50

የጌታ ሥጋ በመቃብር ያደረባቸው ሶስት ቀንና ሌሊቶች፣ በኢየሱስ አቆጣጠር አንድ ሌሊት ነበሩ። ሌሊት ሲሆን ሰው ይተኛል። ሥጋውን ያሳርፋል። ስጋው በእንቅልፍ ውስጥ ባለበት ጊዜ ደግሞ ማንም ሊሰራ አይችልም።

‹‹ማንም ሊሠራ የማይችልባት ሌሊት ትመጣለች።›› ያለውም ይህንን ጊዜ ሲያመለክት ነው። ምንም እንኳ ከሁላችን ጋር ሲነጻጸር ያለ ሥራ በእንቅልፍ የቆየበት የኢየሱስ ሌሊት እጅግ በጣም አጭር ብትሆንም ያው ሌሊት ነበረች።

የሌሊት ማብቂያ፣ የሥጋ አካል ማረፊያ ፍጻሜ፣ ከእንቅልፍ መንቃትና ሌላ አዲስ ቀን መጀመር እንደሆነ ሁሉ የኢየሱስም አጭር ሌሊት ከሶስት ቀናት በኃላ በትንሣኤው

ተደምድሟል፡፡ ሥጋው በማያልፍ ሕይወት ኃይል ተቀስቅሷል፡፡ እየሱስ ነቅቷል፡፡ ጌታ ጊዜው አሁን ቀን መሆኑን፣ ማንም ሊሰራባት የማይችልበት ሌሊት እንደምትመጣ እርሱም በዓለም ሳለ የዓለም ብርሃን እንደሆነ የተናገረው አይነስውሩን የማብራት ምልክት ባደረገ ጊዜ ብቻ አልነበረም፡፡

አይሁድ ሊወግሩት ፈልገው ሳለ ከእጃቸው ወጥቶ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ርቆ በዮርዳኖስ ወንዝ አካባቢ ከከረመ በኃላ ባለበት ስፍራ የወደዳጁ አልአዛር መታመም መልእክት ደረሰው፡፡ ጌታ አልአዛር መታመሙን ብቻ ሳይሆን እንደሚሞትም ያውቅ ነበር፡፡ ሆኖም እንደ አይነ ስውሩ መብራት ሁሉ የአልአዛርም ከሞት መነሳት በእስራኤል ሕዝብና በአይሁድ መሪዎች መካከል የሚፈነጥቀው ታላቅ ብርሃን እንዳለ ስለሚያውቅ ለደቀመዛሙርቱ ‹‹ኑ ወደ አይሁድ እንሂድ አላቸው፡፡›› መምህር ሆይ አይሁድ ከጥቂት ጊዜ በፊት ሊወግሩህ ይፈልጉ ነበር ደግሞም ወደዚያ ትሄዳለህ? ባሉት ጊዜ የመለሰወ መልስ ቀደም ሲል ባየነው ክፍል ስለ ቀንና ሌሊት ከተናገረው ጋር ተዛማጅ ሆኖ እናገኘ ዋለን፡፡

> ‹‹ኢየሱስም መለሰ ቀኑ አሥራ ሁለት ሰአት አይደለምን? በቀን የሚመላለስ ቢኖር የዚህን ዓለም ብርሃን ያያልና አይሰናክልም በሌሊት የሚመላለስ ቢኖር ግን ብርሃን በእርሱ ስለሌለ ይሰናከላል አላቸው፡፡›› ዮሐ. 11፡ 9-10

ጌታ ኢየሱስ በይሁዳ መመላለሱን ያቆመው አይሁድ ሊወግሩት ስለፈለጉ ነው፡፡ እንደደቀመዛመርቱ አመለካከት ይህ ሁኔታ ስላልተለወጠ ወደ ይሁዳ መሄድ አይታሰብም፡፡ ጌታ ኢየሱስ ግን ቀኑ አስራ ሁለት ሰዓት ነው፣ ስለዚህ ሌሊቱ ቢቃረብም ገና አልጨለመም ወደ ይሁዳ በመሄድ መሥራት ለአይሁድ ሕዝብም ማብራት አለብኝ ማለቱ ነው፡፡ ይህን ያለው በይሁዳ አውራጃ በምትገኘው ከኢየሩሣሌም ከተማ 3 ኪሎ ሜትር ርቃ ባለችው በቢታንያ አልአዛርን ከሙታን በማስነሳት የሚሠራው ሥራ ለብዙ አይሁዳውያን የመውደቅና የመነሳት፣ የመዳንና የመጥፋት ምክንያት እንደሚሆን ስለሚያውቅ ነው፡፡ የአልአዛርን መነሳትና ተከትሎ የመጣውን ማመንና መቃወም ስንመለከት የዚህን አባባል እውነተኘነት መገንዘብ እንችላለን፡፡

> ‹‹ከአይሁድም ብዙ ሕዝብ በዚያ እንደነበር አወቀው መጡ ከሙታንም ያስነሳውን አልዓዛርን ደግሞ እንዲያዩ ነበር እንጂ ስለ ኢየሱስ ብቻ አይደለም፡፡ የካህናት አለቆች አልዓዛርን ደግሞ ሊገድሉት ተማከሩ ከአይሁድ ብዙዎች ከእርሱ የተነሳ ሄደው በኢየሱስ ያምኑ ነበርና፡፡›› ዮሐ *12፣9-11*

የኢየሱስ የምድር ኑሮ ቀን መፍጠር የሚችል ብርሃን ነበር፡፡ ብርሃኑም የሰዎችን የሕይወት ጓዳ የሚገልጥ የሕይወት ብርሃን ነበር፡፡ የአይሁድ አለቆች በሥራው እስከሞት ድረስ የተቆጡበት ዋና ምክንያት ሥራው በብዙ ሥርዓትና አሸንክታብ ሸሽገው የያዙትን፣ ካለመገለጡም የተነሳ ከብዙዎች ክብር እየተቀበሉ የሚኖሩበትን ውስጣዊ ማንነትና ነውር የሚገልጥ ብርሃን ስለነበር ነው፡፡

ጨለማ ውስጥ ተሸሽጎ ነውርና ፀያፍ ተግባር እየፈፀመ ያለ ሰው ድንገት መብራት ቢያበሩበት እንደሚበሳጭ ሁሉ ተበሳጩ፡፡ ብርሃኑንም ለማጥፋት ተጣደፉ፣ ሙከራቸውንም ለማጽደቅ ምክንያት ፈለጉ፡፡

‹‹ብርሃን ወደ ዓለም ስለመጣ ሰዎችም ሥራቸው ክፉ ስለነበርና ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ስለወደዱ ፍርዱ ይህ ነው። ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላልና ሥራዉም እንዳይገለጥ ወደ ብርሃን አይወጣም።›› *የሐ 3:19-20*

ጌታ ሰዎች ምንም ያህል ብርሃንን ቢጠሉ ያለ ሰዓቱ ፀሐይ እንድትጠልቅ ሊያደርጉ እንደማይችሉ ሁሉ እርሱንም ሰዓቱ ሳይደርስ አንዳች ሊያደርጉት እንደማይችሉ ለማስረዳት ለደቀመዛሙርቱ፡-

‹‹ቀኑ አስራ ሁለት ሰዓት አይደለምን? . . .››

በማለት ቀኑ ብርሃን የሚሆንበት ሰዓት በእግዚያብሔር የተወሰነ መሆኑንና ያለ ሰዓቱ ማንም አንዳች ማድረግ እንደማይችል ሲነግራቸው እናያለን። ማንም ቀንን ወደ አሥራ አንድ ሰዓት ሊያሳጥረው ወይም ወደ አስራ ሶስት ሰዓት ሊያስረዝመው እንደማይችል ሁሉ አይሁድም ሆኑ ሮማውያን አለ ጊዜው አንዳች ሊያደርጉ አለመቻላቸውን ያሳየናል።

ለዚህ ማረጋገጫው አይሁድ ሊገድሉት ብዙ ጊዜ ፈልገው ሊያደርጉት አለመቻላቸው ነው። ቀደም ብለው ጌታን አለመግደላቸው ለመግደል ስላልፈለጉ ሳይሆን ጊዜው በለመድረሱ መሆኑን ከዚህ ክፍል መረዳት እንችላለን።

‹‹ኢየሱስ በመቅደስ ሲያስተምር በግምጃ ቤት አጠገብ ይህን ነገር ተናገረ። ጊዜው ገና አልደረሰምና ማንም አልያዘውም።›› *ዮሐ 8:20*

እንግዲህ ኢየሱስ ስለ ቀንና ሌሊት የተናገረውን አድርጐም ያሳየውን አስደናቂ እውነት በእነዚህ ሁለት ክፍሎች ተመለከትን። ሆኖም ከሕይወታችን ጋር ሳናዛምደው ብናከትም በረከቱ ሙሉ አይሆንምና ለእኛ ያለውን ተግባራዊነት አንድ በአንድ እንመልከት።

- ጌታ ኢየሱስ በምድር በነበረበት ወቅት በዓለም ሳለሁ የዓለም ብርሃን ነኝ እንዳለ እኛም በዓለም ሣለን የዓለም ብርሃን እንደሆንን እንወቅ ብርሃናችንንም በሰዎች ሁሉ ፊት እናብራ። ብርሃናችን እንዳይታይ የማከለክለውን ግርዶሽ ሁሉ እናስወግድ።

  እናንተ የአለም ብርሃን ናችሁ . . . መብራትን አብርቶ ከእንቅብ በታች አይደለም እንጂ በመቅረዝ ላይ ያኖሩታል በቤት ላሉ ሁሉ ያበራል።

- ብርሃናችን የምንሠራው በጐ ሥራ እንደሆነ እንወቅ በመንፈስም ሆነ በሥጋ፣ በፀጋም ሆነ በችሎታ ከእግዚያብሔር በተሰጠንና በእጃች ባለው ሁሉ ለሌሎች መልካም ሥራን ለመስራት አንታክት። በዙሪያችን ላሉ ሰዎች ቀን እንፍጠርላቸው።

  ።‹‹መልካሙን ስራችሁን አየተው በሰማይ ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ሁሉ ፊት ይብራ።።።›› ማቴ. 5:16

- ጌታ ኢየሱስ በራሱ ዘመን በሥጋው ወራት የዓለም ብርሃን ሆኖ ቀን ፈጥሮ ቀኑን ፈጽሞ ሄዷል አሁን በምድር ላይ በቀጥታ ባያበራም በተዘዋዋሪ መንገድ ግን

ያበራል፣ ያም መንገድ እኛ እንደሆንን በእኛ ውስጥ እንደሚኖር፣ እንደሚሠራና በፈቀድልነት መጠን እንደሚያበራ እንወቅ።

‹‹በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል። እኔ ወደ አብ እሄደለሁ . . . እኔ አደርገዋለሁ።›› ዮሐ. 14፡ 12-14

- በዙሪያችን ያለውን ጨለማ ለመግፈፍ የግድ እውር ማብራትና ሙትን ማስነሣት አይኖርብንም። በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ክርስቶስ በእኛ አድሮ የሚሠራው ማንኛውም በጎ ሥራ የማብራት ኃይል እንዳለው እንወቅ።

- ኢየሱስ በሥጋ በምድር ባለመኖሩ ጨለማ በዋጠው ዓለም ውስጥ ፀሐይ መሆን ባንችልም አንኳ ፀሐይ ዳግመኛ እስክትወጣ ድረስ ከፀሐይ ጋር ህብረት በማድረግ የምናገኘውን ብርሃን በጨለማ በማብራት የሌሊት ጨረቃ እንሁን። በሌሊትም ላይ እንሰልጥን።

‹‹እግዚአብሔርም ሁለት ታላላቆች ብርሃናትን አደረገ ትልቁ ብርሃን በቀን እንዲሰለጥን፣ ትንሹ ብርሃን በሌሊት እንዲሰለጥን . . . አደረገ።
ዘፍ 1:16

- ማብራታችን መልካም ቢሆንም ሁሉን ያስደስታል ብለን አንጠብቅ። እንዲያውም የሚያስቀጣቸውና የሚያበሳጫቸው ሊኖሩ እንደሚችሉ እናስብ። ሆኖም የፈለገውን ያህል ቢቃወሙንም ጊዜው ሳይደርስ ምንም ሊያደርጉን እንደማይችሉ እንወቅ። የፈለገ ቢሆን ያለ ቀናችን ልናንቀላፋ፣ ሰዓቱም ከደረሰ ልናዘገየው አንችልምና። በክፉዎች ዛቻ በፍርሃት አንናወጥ። እንደደረሰበት መከራና የሞት አደጋ ሐዋርያው ጳውሎስ በአገልግሎቱ አጋማሽ በሞተ ነበር። ነገር ግን ክርስቶስ በውስጡ የሚያበራ ሰው ሰዓቱ ሳይደርስ አይጠልቅምና እኛም ካልዛልን በቀር ሩጫችንን ለመጨረስ በቂ ጊዜ እንዳለን እንወቅ።

‹‹. . . ዳሩ ግን የስብከቱ ሥራ በእኔ እንዲፈፀም አሕዛብም ሁሉ እንዲሰሙት ጌታ በእኔ አጠገብ ቆሞ አበረታኝ። ከአንበሳ አፍም ዳንኩ። ጌታም ከክፉ ነገር ሁሉ ያድነኛል ለሰማያዊውም መንግስት ይጠብቀኛል ለእርሱ ከዘላለመ እስከ ዘላለም ክብር ይሁን አሜን።›› 2ጢሞ 4:17፡18

- ጌታ ማንም ሊሠራባት የማይችል ሌሊት ትመጣለች እንዳለ መንፈሳችን ከሥጋችን ወጥቶ አንዴ ሥጋችን ካንቀላፋ ጌታ ዳግም መጥቶ በትንሣኤ እስኪቀሰቅሰው ድረስ በእንቅልፍ ያሸልባል እንጂ ልንሰራበት አንችልምና ዛሬ ቀን ሳለ ባለን አቅምና ጉልበት ሁሉ ለመሥራት እንትጋ። ነገ መሥራት እንደማንችል እያሰብን ዛሬ ቀን ሳለ ሥራችንን እናጠናቅቅ እንጂ ፊፅሞ ለነገ አንቅጠር ስጋችንን በምድር ትተን በሰማይ ስናድር ጌታ ያገለግለናል እንጂ ጌታን አናገለግልም፣ በጌታ እናርፋለን እንጂ በዚያ ለጌታ እንደማንሰራ እንወቅ። ሥጋችን በአፈር ውስጥ የሚቆይበትን ዘመን አናውቅምና ዛሬ ለጌታ መሥራት ስንችል በሙሉ ልባችን በሙሉ ሃይላችን እንሥራ፣ እናገልግል።

- እኛ ከምድር ስንሄድ አንድ ብርሃን እንደሚጎድልና ጨለማው እንደሚበረታ እናስብና በሕይወት እያለን ሌሎች አብሪዎችን እንተካ፡፡ ጌታ ከምድር እንደሚሄድ አውቆ አልተቀመጠም፣ እርሱ ሲሄድ በምድር እርሱን ወክለው የሚያበሩ ከዋክብትን ለመትከል ቀንና ሌሊት እንደሠራ እኛም ጊዜያችንንና ጥሪታችንን ጠፊ ቁሳቁስና አላፊ ኘሮግራም ላይ ሳይሆን ኗሪ ሰዎች ላይ፣ ተተኪ ትውልድ ላይ እናውል፡፡

እንግዲህ ዘመን  እየተቀየረ ነው፡፡ 1999 ዓ.ም. ወደ ሁለት 2000 ተቀየረ ሁለት ሺህ ደግሞ  አሁን ወደ ሁለት ሺህ አንድ በመሸጋገር ላይ ይገኛል፡፡ እኛም በሥጋ በምድር ላይ አለን፣ ስለዚህ ቀን ነው ማለት ነው፡፡ የቀኑም ምክንያት እኛ እንደሆንን ወይም መሆን እንዳለብን እየተረዳን ብርሃናችን የሆነውን ክርስቶስን እናብራ፡፡

‹‹በመጥፎና በጠማማ ትውልድ መካከል ያለ ነቀፋ የዋሆችም ነውርም የሌለባቸው  የእግዚያብሔር ለጆች እንድትሆኑ ሳታንጎራጉሩ ክፉም ሳታስቡ ሁሉን አድርጉ በእነርሱ መካከል /በመጥፎና በጠማማ ትውልድ / የህይወትን ቃል እያቀረባችሁ በዓለም እንደ ብርሃን ትታያላችሁ . . .፡ ›› ፊሊ 2፡ 14-15

መልካም ቀን !

ያሬድ ጥላሁን
የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ